# ካለበት የተጋባበት

ይነጋል በላቸው

*ደም መራዥ ልጅ - ያፋፍ ድጥ ... ያሽሙር ደለል፤*
*የወሬ ማንፈሻ ጋሻ ደርሼለት እርሱን መሰል፤*
*በተከለው እሚተክል...*
*አባቴስ ወንድ ወለድኩ ይበል፡፡*

የአማርኛው ብሂል ‹ካለበት የተጋባበት› ይለዋል፡፡ ፈረንጅኛውም ለዚህ ዓይነቱ አባባል ከአማርኛው አይሰንፍም፤ More catholic than the Pope በማለት ያሳምረዋል፡፡ እንዲህ ዓይነት አባባሎች ከአፎታቸው ተመዝዘው ወደ ደንበኞቻቸው እንደጃርት ወለባ እየተወረወሩ እሚሰኩት ኃይለማርያም ደሳለኝን የመሰለ ራሱን መሆን የማይችል በጥቅም ወይም በዓላማ ወይም በአእምሮ ዘገምተኝነት ወይም ምናልባትም በነዚህ በሦስቱምና በሌሎችም ተዛማጅ ምክንያቶች የተነሣ ሰውነቱን ለባዕድ ስብዕና ያስገዛ አስገራሚ ፍጡር ሲያጋጥም ነው፡፡ ለነገሩ ዘመኑ የአስገራሚ ፍጡራን መናኸሪያ ስለሆነ አሁን አሁን የሚያስገርመን ይልቁናም ደህና ሰው ያገኘን እንደሆነ ነው፡፡ ምክንያቱም በ‹ኩኑ ከማሆሙ› የአባትህ ሀገር ሲወረር አብረህ ውረር ፈሊጥ (ለዚህም ፈረንጆቹ ከዚያው ከጣሊያን ያልወጣ መሰል አባባል አላቸው - When you are in Rome do as the Romans do.) ሕዝበ አዳም ይሉኝታውንና ባህል ሃይማኖቱን አሽቀንጥሮ ጥሎ ወቅቱ ለሚፈልገው ኑሮን በየትም ፍጪው ዱጨቱን አምጪው በአቋራጭ የማለፍ ዘመን አመጣሽ ወረርሽኝ በመገዛቱ በዚህ ዘመን ደጋግ ሰዎችን ለማየት ብዙም አልታደልንም፡፡ እስከመቼ በዚህ መልክ እንደምንጓዝም አንድዬ ብቻ ነው የሚያውቀው፡፡ የመልቲዎች አበቅቴ ግን እያለቀ ለመሆኑ ብዙ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡

በትናንትናው ዕለት  የቁጩው ጠቅላይ ሚኒስትራችን - እንዴት ይቀፈኛል እንዲህ ስል እባካችሁ - ‹ያልወለድኩት ልጅ ቢለኝ አባባ አፌን አለው ዳባ› አሉ - አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በመለስ አሻንጉሊት ፓርላማ ተገኝቶ ጥያቄዎችን ሲመልስ ለተወሰኑ ደቂቃዎች አድምጫለሁ፡፡ ለዚህች ማስታወሻ የሚበቃኝን ያህል ካዳመጥኩ ሌላው እንቶ ፈንቶ ምን ይሠራልኛልና በጊዜየና በጆሮየ ልቀልድ? የዚህን ሰውዬ ንግግር እንዳዳመጥኩ የመጀመሪያው ትዝ ያለኝ ነገር በመግቢያየ ላይ ቀንጭቤ ያስቀመጥኳት የፀጋዬ ገ/መድኅን ዋቀዮ ግጥም ነው፡፡ እናም አልኩ - መለስ አፈሩን ገለጥ አድርጎ ቢመለከት ምንኛ በደስታ ተውጦ በፈነጠዘ! ኢትዮጵያን የማጥፋት ዓላማው በጅምር አለመቅረቱንና ለዚሁ ተግባር ያሠለጠናቸው ‹ሹምባሾችና ሙንጣዢች› በየስብሰባው - የሙት መንፈሱ የሚያያቸው እየመሰላቸው - በነዚያ ‹የሚያማምሩ ቅንድቦቹ›ም በቁጣ የሚመነትጋቸው መስሎ እየታያቸው -  ጠብ እርግፍ ሲሉለት ሲያይ ምንኛ ይደሰት! የዘሩት ሲያፈራ፣ የተከሉት ዱባና ቅል - እምባጮና ሰንሰል ለአገልግሎት ሲደርስ ደስ ይላል፡፡ የመለስ ጀምበር የጠለቀች ብትመስልም የአነጋገር ቅላፄውን ሳይቀር በኮረጁ አንጋፋና ወጣት ልጆቹ ስሙ እንደውዳሤ ማርያም ሠርክ እየተደገመ፣ ለነሱ ግልጥ የሆነው የልማት ሥራው ዘወትር እየተወሳ በሕይወት ያለ ያህል አለ፡፡ እንዲያውም ‹ስሙን አታንሱ፣ ሥራውን አታውሱ…የምትሉን ቀይ መስመር እያለፋችሁ፣ ሁለት ባርኔጣም እየደፋችሁ ነውና ዕረፉ!› በሚል ማስጠንቀቂያ እየተወረፍን ነው - ካለበት የተጋባበት ማለትም ይሄውና ይሄው ብቻ ነው - አራት ነጥብ፡፡ ኃይለማርያም በመልክ ብቻ ሳይሆን በአነጋገርም ቁርጥ ቁምጥ መለስን እየሆነ ነው - ግን ልፋ ብሎት እንጂ ወቅቱ ሲደርስ መለስን አለመሆኑን ይረዳል፡፡ ግዴላችሁም ለዚህ ሰውዬ - ለመለስ ዜናዊ - 45ኛ ጽላት ተበጅቶ በአቡነ ናትናኤላቸው ተባርኮ ሕዝብ እንዲሰግድ ሳይደረግ አይቀርም፡፡ ኢትዮጵያ የትንግርት ሀገር መሆኗ ካልቀረ አረማዊው መለስ - በእግዚአብሔር ኀልውና የማያምነው ለገሠ ዜናዊ ታቦት ይቀረጽለትና እኛም ትንሽ እንሳቅ ሕዝበ መለስም ሄዶ ‹ያፈንድድለት› ማለቱ እንኳን ይቅርብኝ ‹ይስገድለት› ልበል በጨዋ አነጋገር፡፡ ስግደት ሲያንሰው ነው፤ የመቶ ዓመት የቤት ሥራውን በ21 ዓመታት ውስጥ

አገባድዶ ሀገሪቱን የለየላት የጥቂት ደናቁርት መፈንጫ ያደረገ አሰለጥ ሰው ቤተ አምልኮ በስሙ ተሠርቶ መሰል ደናቁርት ቢያመልኩት - ነጋ ጠባ ቢሰግዱለት ጥሩ መታሰቢያ ነው። ሰውን የሚያመልክ ሁነኛ ሃይማኖት የሌለው ከርሳም ነውና ሆዳሞች ሚችን ቢያመልኩ አይገርምም።

የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ኃይለ ማርያም የተረከባት ኢትዮጵያ - አይ አማርኛ - ኃይለማርያም የተረከባት ኢትዮጵያ - አልኩ አይደል? እባካችሁ የተነሳሁበት አንቀጽ ይቅርና በሌላ አንቀጽ ወደዚህ ሰውዬ ልግባ።

ለመሆኑ ኃይለማርያም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ነውን?

እንደማስታወሻ፡- ከዘርም ሆነ ከኢትዮጵያዊነት አንጻር ኃይለማርያም የኢትዮጵያ ቀርቶ የዓለም መሪ ከመሆን የሚያግደው ነገር የለም። በትምህርትም ጥሩ ደረጃ ላይ የደረሰ ነው። በልምድም አይከፋም። ነገር ግን የተገኘበት ቦታ የምር ቦታ ሳይሆን የቀልድ ቦታ ስለሆነ ነው ‹ሥልጣኑን› በብዕሬ እያላገጥኩበት የምገኝበት ሁኔታ የተፈጠረው። ምድረ አሽሙረኛ፣ ሰውዬው የዚህ ወይ የዚያ አቅጣጫ ሰው ስለሆነ ወይ ስላልሆነ ነው እንዲህ የሚቀልድበት እንዳትይ! ራስሽ ነሽ የምትኮነኛት። ኃ/ማርያም በዚህ ሥፍራ የተገኘው በፍጹም አጋጣሚ ነው፤ ያኛው ሞኙ ሰውዬ - ያ የሀገሩ መሬት ለሰው ሀገር እንዲሰጥ ወያኔ፣ ጡት እንዳልጣለ ሕጻን እጁን ጎትቶ አስፈርሞታል የሚባልለት ደመቀ መኮንን የሚባለው ጅል - ከዚህ በላይ ቃል መጠቀም ስለሚያነውረኝ ነው - በእናቱ ማኅፀን ውኃ ሆኖ ቢቀር የሚሻለው የታሪክ ወበሎ ነው። ይሄኛው ጅል፣ ጠላቱ ሞኝነቱና ተምሮ ያለመማሩ እንጂ በአማራ ላይ ጥላቻ ኖሮት አይመስለኝም። ያኛው ግን - የኢየሱስን ቃል በሀሰት ለውጦ ጣዖት አምላኪ የሆነው ኃይለማርያም ማለት ነው - በመለስ ተበጥብጦ የተወጋው በተለይ የአማራ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ጥላቻ አለበት ይባላል፤ እርግጥ ይህን ሀሜታ ማረጋገጥ ሊኖርብን ይችላል፤ ይባላልን እንዳለ መውሰድ አደገኛ ነውና።

የኢትዮጵያን ፖለቲካ በማንቀራበጥ አኳያ ከጅኦግራፊው ባልተናነሰ ጥርሳቸውን የነቀሉበት ፕሮፌሰር መስፍን ወ.ማርያም በትናንትናው ምሽት ለኢሣት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ በሰጡት ቃል ይህ ሰውዬ ራሱን እስኪሆን ትንሽ ጊዜ እንስጠው ማለታቸው ምን ማለታቸው እንደሆነ ግር ብሎኛል። ቡፍጹም አልገባኝም። አሁን ማን ይሙት ኃይለማርያም ከእንግዲህ - ሁለትና ሦስት ፀጉር ካበቀለ በኋላ - ከመለስ ክርታስ(ሼል) ወጥቶ የራሱ ስብዕና ይኖረዋል? ለምን ይዋሻል ማለት አሁን ነው። ፕሮፌሰር ይጠየቁልኝ - ለዲፕሎማሲያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ነው ወይንስ ከምራቸው? እውነታቸውን ከሆነ ከአሁን በኋላ ከእባብ ዕንቁላል እርግብ ሊፈለፈል እንደሚችል መጠበቅ ቂልነት መሆኑ ሊቀር ነው ማለት ነው። ኃይለማርያም ማለት የትሮይ ፈረስ ነው፤ ኃይለማርያም ማለት መናጆ ኮርማ ነው። አንድ ለእርሻ ወይም ለሽያጭ የሚነዳ በሬ አልሄድም ብሎ እንዳይለግም ሌላ መናጆ(ዎች) አብሮ እንዲሄድ ይደረጋል። የሚፈለግበት ቦታ ላይ ሲደርስ ግን መናጆው ወደቤት ይመለሳል። ሥራው ያኛው በሬ ወደሚፈለገው ሥፍራ እንዲሄድ ማጀብ ነው። ኃይለማርያም ለመናጆነት ራሱ ‹መታደሉም› የሚያስገርመን ብዙዎች አለን። ያልታሰበ ነው። ስንትና ስንቶች ለወያኔያዊ የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች ቅርብ የሆኑ መናጆዎች ሞልተው ሳለ በመለስ ባለመታመናቸው ምክንያት ብቻ - ከመናጆነት ባለፈ ለሥልጣን ንጥቂያው ይገዳደራሉ ከሚል ፍራቻ የተስፈነጠሩ ሞልተዋል - አሁን ውስጥ ውስጡን በቁጭት እየበገኑ ያሉ - ከወያኔ ውድብ ከወጡትም ካልወጡትም። ቁጭታቸው ሥልጣን በነሱው እሳቤ ደቡብ መግባቱ አይደለም - አለመግባቱን ያውቃሉና። ግን ውሻ በቀደደው ጅብ(እነእንትና ለማለት ነው) እንዳይገባና ይህችን ማርና ቅቤ የሚታፈስባትን ኢትዮጵያ ከብቻ ቁጥጥር እንዳያወጣባቸው ከወዲሁ በመስጋት ነው - ለዚህ ነው ለብቻ ሲሆኑ መለስን የሚወቅሱት ‹ወይ እዙይ ለቁማጽ አዋሪዱና› እንደሚሉ እገምታለሁ - ሳያዘጋጃቸው ዐይናቸውን እንዳልገለጡ የዶሮ ጫጩቶች ሜዳ ላይ በቶኖኣቸው በመሞቱ። ማንም ወያኔ ይወቅ! የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ ከእንግዲህ ሱሚ ነው፤ የለም። የቀን ጉዳይ እንጂ ኢትዮጵያ ወደኢትዮጵያውያን እጅ ልትመለስ የቀረው ጊዜ በጣም አጭር ነው። አቡሻክሩ ሲነበብ ይህን ያረጋግጣል፤ ጉዞ ወደተስፋዋ ምድር ሊጀመር ነውና በስደት ያላችሁ ተዘጋጁ። አሜን! ሃሌ ሉያ! አንዳንዴ እንደመሪያችንም ያደርገኛል ልበል? (በነገራችን ላይ ፍቅርና እውነት የሌለበት ማንኛውም ሃይማኖት፣ ሃይማኖት ሳይሆን ማርክስ ይሁን ሌኒን እንዳሉት በርግጥም የመበዝበዣ መሣሪያ ነው። መልካምነት፣ ፍቅርና

እውነት የሰው ልጆች አጠቃላይ ሃይማኖት ቢሆኑ ኖሮ ይህን ያህል ትርምስና ሁከት በዓለማችን ላይ ባልተከሰተ ነበር፡፡ ሰው እየጨነቀው በሺዎች ሃይማኖቶች እየተባደነ በ‹ከባልሽ ባሌ ይበልጣል…› መናቆርንና መተላለቅን ወደደ እንጂ ሁሉም ወደ እውነት ቢመጣ የሰው ልጅ ሃይማኖት ከአንድ ሊበልጥ ባልተገባ! እሱም - እስላም ወይ ክርስቲያን የምል እንዳይመስላችሁ - እሱም 'Goodness' ነው፡፡ መልካም ሁን፤ ሰዎችም ለአንተ መልካም ይሁኑልህ፤ አፍቅር - ያፍቅሩህ - ፍቅር ሲባል በተለምዶ ወደአእምሮኣችን ቀድሞ የሚመጣልን - አንዳንዴም በዐይነ በሲርነት የሚገለጠው የወንድና የሴት ፍቅር አይደለም፡፡ ፍቅር የምንለው በፈረንጅኛው አጠራር Platonic Love ወይም/እና Agape(አጋፔ) የሚሉት ነው፡፡ ይህ ካለን የታመመንና የደከመን ሰው ሰላም እያሳጣን የሰማይን በሮች በደጅ ጥናት ብዛት መክፈት ላይቻለን 24 ሰዓት ላንቃችን እስኪበጠስ በጸሎት መጮኽም ሆነ በዕንባ እየታጠቡ ሥርየትን ለማግኘት ጊታርና ፒያኖ መደለቅ አያስፈልገንም፡፡ ያኔ ‹የኔ ሃይማኖት ተነካ፤ የነሱ እንዲህ ሆነ› ማለት ይቀርና ሰብኣዊነት ላይ የተመሠረተ ወርቃማ የፍቅር ዓለም መገንባት ይጀምራል፤ ያኔ አንዱ የሁሉም ሁሉም ያንዱ ይሆናሉ፤ ፈጣሪም የብርሃን ፊቱን ይመልስልናል፡፡ አለበለዚያ እመኑኝ ድካም ነው ትርፋችን፡፡)

ንግባኢኬ ሃበ ጥንተ ነገር - ወደቀደመው ነገራችን እንግባ - በቅርቡ ‹ወደገደለው› የሚል አማርኛም መጥቷል፡- ይህ ሰው ከምኑም ከምኑም ሳይኖርበት - ከበረሃ ሳይመጣ፣ በአምቻ ጋብቻ ከእነእንቶኔ ጋር ሳይቆላለፍ - ሳይተግር - ሌላም ጨምሩበት ከፈለጋችሁ - ለመለስ የአምባገነን ጠባይ ስላመቸ ብቻ በርሱ ትዕዛዝ እንደልብ ለሚከናወኑ የም/ጠ/ሚኒስትርነትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ቦታዎች ያኔ ይህ ጉድ ይመጣል ተብሎ ሳይታሰብ እንደቀልድ ‹ተሾመ›፡፡ ነገሩ ተብሎ ተብሎ ያለቀ ቢሆንም ሀገራዊ እውነቱን ስንገርበው ከዚህ ውጪ የሚያፈናፍነን የለም፡፡ ሃቁ ይሄውና ይሄው ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ሰው መቶ ዓመት ቢሰጠውም የራሱን ማንነት ሊያገኝ አይችልም፡፡ የራሱ ማንነት በሣተናዎቹ የወያኔ የደኅንነትና የጦር አባላት እጅ ውስጥ ተከርችሟል፡፡ ራሱን ለመሆን በፈለገ ማግሥት ራሱን የሚያገኘው አንድም ከርቸሌ ነው፤ አንድም ዮሴፍ የመቃብር ቦታ ነው(ከዚህስ ይሠውረው)፤ አንድም በባሌ ወይ በቦሌ ወጥቶ ለስደት መዳረግ ነው፡፡ ቀልድ ነው እንዴ በወያኔ ዘመን ራስን መሆን? ምን ማለታችሁ ነው - እንኳን እሱ ይነጋል በላቸውም ራሱን አልሆነም - እንደሱው የውሸትም ይሁን የእውነት ምንም ሥልጣን የሌለኝው ተራው ዜጋ - እንዳለማየሁ ሞገስ አባባል ጎጋው ዜጋ ማለቴ ነው፡፡ ወያኔ እያለች ወያኔን ሆነህ ወይም ቢያንስ መስለህ ነው በኢትዮጵያ ውስጥ መኖር የምትችለው፡፡ እንዴ! በዐዋጅ የሚለቀስበትና በትዕዛዝ ሰደቃና ተዝካር ለሟች ጠቅላይ ሚኒስትር የሚደገስበት ሀገር ውስጥ ተቀምጦ የምን ራስን መሆን የሚሉት ፈሊጥ ነው? ራሱን ሆኖና ራሱን የሚመስሉ የጭልፊት ጫጩቶች ፈልፍሎ የ‹ኖረ›ና የሞተ መለስ ዜናዊ ብቻ ነው፡፡ የየቁጫጩን የወያኔ የቀበሌ ካድሬ ሲናገር ብትሰሙት እኮ እነዚህ ሰዎች ሌሊት ሌሊት ጌታቸውን አስመስለው እንዲናገሩ የተቀረጸ ድምጹን ከፍተው ሲለማመዱ ያድሩ ይሆን ትላላችሁ፡፡ ድምፀቱ፣ ቅላጼው፣ ጉራውና ትዕቢቱ አይሄድ አይመጣ ቁርጥ የመለስን! ለማንኛውም የግፍ አገዛዝን አለመቃወም በራሱ አድርባይነትና ከአካባቢ ጋር ተመሳስሎ ቁዝምዝምን የማሳለፍ ዘዴ በመሆኑ ብዙዎቻችን ወደፊት ቢያንስ በንስሐ የምናወራርደው ኃጢያት አለብን፡፡ ብቻ ለንስሐ ሞት ያብቃን፡፡

ሳልረሳው እናንተዬ - ኢሣት ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል - እልልልልልል…፡፡ ‹ትልቅ ጦር ባይወጉበት ያስፈራሩበት› ይባላል፡፡ በጣም ተደስተናል፡፡ አማራጭ የዜና ማዕከል በማግኘታችን ወያኔ ብቻውን አይፈነጭብንም፡፡ ዋናው ያዝልቅልን ነው፡፡ በነገራችን ላይ ኢሣትን ለማስገባት ናይል የተባለውን ሳተላይት በአዲስ መልክ ፈልጎ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ ያን ለማድረግ በአማካይ 100 ብር ለባለሙያ መክፈል ይጠበቃል፡፡ በመቶ ብር ቀርቶ ያለው ሰው ከዚያም በላይ ከፍሎ ኢሣትን ማግኘት እጅግ አንገብጋቢ ወቅታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ግን ወደናይል ሲዞር ሲኤን ኤንንና ብሉምበርግን የመሳሰሉ በአረብ ሳት የማይገኙ በርካታ የዜና፣ የእስፖርትና የፊልም ጣቢያዎችን ማግኘት የመቻሉን ያህል ቪኦኤን ግን ማግኘት አልተቻለም፡፡ ስለዚህ ይህችን ቅሬታ ትሁን ጥቆማ ራሳችሁ ስም ስጧትና ለቪኦኤ የሚያደርስልን ብናገኝ በከፍተኛ ምሥጋና ወሮታችንን እንከፍላለን - ልብ አድርጉ ወሮታው ምሥጋና ነው - ግን ከፍተኛ! ቪኦኤዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ - ዝግጅታቸው በአረብሳት እንዳለ ሁሉ በናይል ሳትም እንዲገባና ወደኢሣት እየተገለበጠ ያለው ሕዝብ እነሱንም

እንዲከታተል ሊያደርጉ የሚቻላቸው ይመስለኛል- ሊያውም በቀላሉ። ጉዳዩ መረጃን ካለማግኘት ካልሆነ በስተቀር ከባድ አይመስለኝም። ‹እስመአልቦ ነገር ሰይሰኣና ለአሜሪካ› አይደል የዘመኑስ ብሂል!

ስለዝግጅቶቻቸው ግን በመጣጥፍ መልክ ሳይሆን በራሳቸው ኢሜይል በመላላክ መጨመር ወይም መቀነስ የሚገባቸውን ቅመሞችና መከለሻዎች መነጋገር ይቻላል፤ ‹ጥንካሬያችንን ለሌሎች ድክመታችንን ለእኛ› ይሏት ወርቃማ አባባል በአንዳንድ ልባም ንግድ ቤቶች ደጅ ላይ ተለጥፋ አይቻለሁ - ጥሩ ነው ፤ በአደባባይ ከመወራከብ - ውኃን እንደመውቀጥ ይመስለኛል - ስህተት መስሎ የሚታየንን ነገር በባለጉዳዮች መካከል ብቻ መነጋገርና ቅሬታን ከልብ በመወያየት ማስወገድ ትልቅ ብልህነትና ጨዋነትም ነው። ወፌ ቆመችን እንልመድ ጎበዝ። መናናቅንና ትግስት የለሽነትን ትተን መከባበርንና መቻቻልን ባህላችን እናድርግ። ከእስካሁኑ የመነቃቀፍ ባህል ወጥተን መደጋገፍን፣ በአንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ለአንድ ዓላማ ፀንቶ መቆምን እንለማመድ። ለነቀፋ ብቻ የተሠራን ሰዎች መልካም ነገርን በማሰብና በመናገር የአዲስ አስተሳሰብና አመለካከት ባለቤት በመሆን ሰዎችን ማስተካከልና ወደኛ መሳብ እንደምንችልም እንረዳ። ብዙ የሚያስቀጩ ነገሮች አሉብን። ይህ በሞቶዎችና በሺዎች ቦታ እየተከፋፈሉ መቆራቆስ አሁን ላለንበት የከፋ ሁኔታ ዳረገን እንጂ አንድም ጥቅም አላመጣም። መጽሐፉ እርስ በርስ ተዋደዱ እያለ እኛ ግን ሚዛን በማያነሱ የጎጥና የቋንቋ ተፈጥሯዊ ልዩነቶች ተረትተን ወርቃማ ጊዜያችንን በከንቱ እያባከንን እንገኛለን። ይህ ደግሞ ወያኔን እየጠቀመ እኛን ግን እየጎዳ ያለበት ሁኔታ ተፈጥሮ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው - በራሱ በወያኔዊ አገላለጽ።

በሀገር ቤት ያለው ወገን ነጻነቱን በጉጉት እየተጠባበቀ ይገኛል - ከሰማይም ከምድርም። በዚህን አሳሳቢ ወቅት ታዲያ ልዩነትን ማጥበብና ለሰፊው ሕዝብ ፍላጎት መገዛትን ማስቀደም፣ እንደእስከዛሬው በቡድናዊ ስሜት ታውሮ የኔ ካልሆነ የናንተ ጥንቅር ይበል የሚለው ልማዳዊው የሁልጊዜ አሸናፊነት ስሜት እንደማያዋጣ ማወቅ ይገባል። እኛ ኢትዮጵያውያን መሸነፍን አለመውደዳችን በአንድ ጎኑ ጥሩ ሆኖ በሌላ ጎኑ ግን ክፉኛ እየጎዳን ነው። እንደገታራው ወያኔ ሁልጊዜ በአሸናፊነት ለመውጣት የተሞከረ እንደሆነ ኪሣራ አለው። ተሸንፎ ማሸነፍም አለ፤ አሸንፎ መሸነፍም አለ። ሁልጊዜ እኔው ካላሸነፍኩ ሰማይና ምድር ያልፋሉ የሚል ካለ ተጋጣሚ አይኖረውም - የውድድር መንፈስም ከነአካቴው ይጠፋል፤ ይህ በየትኛውም ጎራ እየጎዳን ያለ ጀብደኝነትና የብልሹ ሥነ ልቦና ውላጅ ካልጠፋ ሀገራችን የነጨቡዴና የነአቶ ተማቹ መንቦራቦሪያ እንደሆነች ትቀራለች። ችግሮች ቢከሰቱና ሲከሰቱ ቁጭ ብሎ በእርጋታ በመነጋገር ለማስወገድ እስከመጨረሻው መጣር ይገባል። በተለይ ሀገር ሳትኖረን ስደት ላይ ሆኖ መጣላትና መጨቃጨቅ ትዝብት ላይ ይጥላል - ያሳፍራልም። ሥልጣን የሚገኘው ደግሞ ከነጻነት በኋላ እንጂ አሁን በምናብ የነፋስ አምባ ላይ የተንጠለጠለ ሥልጣን ሊያጣላ አይገባም፤ ወጡ ሳይወጠወጥ እንዲሉ ይሆናልና። ግዴላችሁም - ሀገር ከተፈጠረች ሥልጣን በሽ በሽ ነው፤ ሞልቷል። እባካችሁን በተቃውሞው ጎራ የተሠለፋችሁ ወገኖች - ‹እንዲህ ልጠግብ በሬየን አረድኩ› እንዳለችው ሴትዮ ከመሆናችሁ በፊት በቀላሉ እየተላለፋችሁ መቀመቅ የወረደ ሕዝባችሁን ድረሱለት። ሥልጣን እሳት ነው፤ የተጠቀለለበት ጥቅማጥቅምና ዝና እያንጓን እንደ እሳት ራት ዘልለን እየገባን ከምናልቅ ትክክለኛው ሰው ለትክክለኛው ቦታ በሚለው ነባር መርህ ሁነኞችን እያዘጋጀን ሀገራችንን ከገባችበት ማጥ የሚታደጉ መሲሖችን እንፍጠር። ደግሞም አንመቀኛኝ። ምቀኝነትን ከባህላችን ሰርዘን እናውጣው፤ ምቀኝነት ክትባትም ሆነ መርፌ፣ የሚቀባም ሆነ የሚታሽ፣ የሚዋጥም ሆነ የሚታኘክ መድሓኒት የሌለው በተለይ በኢትዮጵያ ላይ ክፉኛ ነግሦ የሚገኝ እጅግ አደገኛ በሽታ ነው - እርግጥ ነው መንስኤዎቹ በአብዛኛው ድህነትና ማይምነት እንዲሁም ተጣሞ የሚተላለፍ የመጥፎ ባህል አጉል ቅርስ ናቸው። ለዚህ አብነቱ በዋናነት ራስን በትምህርትና በንባብ ማበልጸግ ነው - ለወደፊቱ አዲስ ጠበል ከፈለቀም እየሄድን እንድንጠበል መጠቆሜ አይቀርም። በእውኑ በዚህ ጉዳይ ሰው እስኪታዘበን ድረስ ተጎድተንበታል። እመብርሃንን ከአንጀቴ ነው የምለው - ምቀኝነትን አፈር ያብላው! ጎጠኝነትማ በደም ትራንስፊዉዥን እንሞክረው እንደሆነ እንጂ አዳሜን በክሎ በክሎ ፖዘቲቭ አድርጎት እየተጫወተብን ነው። በአሁኑ ወቅት ብዙ ሰው በአነጋርህ ወይም በጭንቅላትህና በፊትህ ቅርጽ

እንዲሁም ገጽህ ላይ በሚገኙ የተለያዩ ምልክቶችህ የየትኛው ጎሣ ተወላጅ መሆንህን ካላወቀ ‹ዘርህ ምንድነው?› ብሎ ለመጠየቅ ጊዜ አይወስድበትም። ኃይለኛ ልክፍት ነው፤ ኢትዮጵያዊነት ውራ ወጥቶ ጎጠኝነት ነግሦኣል። አቤት ቀጣዩ የኢትዮጵያ መንግሥት ያለበት አበሳ! ስንት ነገር ተጣሟል መሰላችሁ! ይሁን። ለበጎ ነው። ደግነቱ ግን ይህም ያልፋል።

አሁንም ሆነ ወደፊት ስትሹዋሹዋሙ ደግሞ እንደውሻ ደምና አጥንት እያነፈነፋችሁ አይሁን። እጅግ የሚያስጠላና ከዘመናዊ ሰው የማይጠበቅ አካሄድ ነው። ወያኔ ያባባሰብን - ከበፊትም ግን በመጠኑ የነበረ - ይህ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ነቀርሣ በቶሎ መወገድ አለበት። በችሎታና ብቃት ላይ የተመሠረተ ሹመትና ሥራ አያያዝ እንጂ የዘር ኮታ ሥርዓት በጭራሽ አያስፈልገንም። ይሄ ብሔርና ዘር ያመጣብን ጣጣ በአፋጣኝ ካልተነቀለ ያጠፋናል - እስካሁንና አሁን ጠፍተን ካልሆነ። የኃይለ ማርያም የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ ዓይነት ወያኔዊ ድንፋታ ግን ለጤና ነው ትላላችሁ? እኔን ያንተክትከኝና እንደሽሮ ከላይ ከላይ እየተንተከተከ ደነፋብን እኮ ትናንት! ድንቄም ጠቅላይ ሚኒስትር። ሲዳሩ ማልቀስ ወግ ነው አሉ። በወያኔዎች የቀጥታ ትዕዛዝ ‹ይህን በል፣ ይህን አትበል፣ ይህን ፈርም፣ ይህን አትፈርም› እየተባለ በ‹simulation› የፋገራ ሥልጣን እንዲህ የሆነ ከእውነት ጠቅላይ ሚኒስትራችን ቢሆን ምን ያሳይ ይሆን እባካችሁን? ግን ግን የጠቅላይ ሚኒስትራችን ዐይን እንኳን ሳይፈስ የርሱም ፊርማ ሳይደርቅ ገና ከአሁኑ እንዲህ ይደንፋብን? ዕንባችን ሳይደርቅ - ሀዘናችንን በቅጡ ሳንወጣ - መንፈቁንና ሙታመቱን ሳንዘክር … እንደዚህ በቃላት እሩምታ በላያችን ላይ መዝፈን የሥልጣን ፍቅር አይመስልም? ጌታ ልብ ይስጠው ከማለት ውጪ ምን ይባላል።

ይልቁስ ጌታው ኃይለ ማርያም - ስማኝማ - የማያድሩበት ቤት አያመሹበትም ነውና በጊዜ ጥግህን ፈልግ። ተጨማሪ ኪሣራ ውስጥ ሳትገባ - ለልጆችህና ከራሱ በላይ ዓለምን ወዶ በመስቀል ላይ ተቸንክሮ ስለሞተው የፍቅር አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ስትል ራስህን አድን - ክርስትናህም የውሸት አይሁንብህ - ክርስቶስ ከሀሰተኞች ተጠንቀቁ ብሏልና ለራስህ ስትል ራስህንና የምትገኝበትን ሁኔታ ለመመርመር ጊዜ ይኑርህ ። ስብከት ላይ አይደለሁም። ግን አያያዝህ በጭራሽ አላማረኝም። በያዝከው መንገድ ብዙዎች ነጉደውበት አሁን በሀፍረት ተሸማቅቀው አይኖሩ ኑሮ እየኖሩ ነውና ከነሱ ተማር። ታምራት ላይኔ በቅርብህ የሚገኝ አንድ ምሳሌ ነው። እናም ለሥጋህ ጊዜያዊ ድሎት ብለህ ነፍስህን ከሚያጠፉ የወንበዴዎች ኅብረት ጋር ሊያውም በመጨረሻው ዘመናቸው መደመርህ ላንተ መልካም አይደለምና በአፋጣኝ ውጣ። የክርስቶስን አነጋገር ተጠቅሜ አንድ መልእክት እንድናገር ይፈቀድልኝና በሰው ላብቃ፤ “እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ኢትዮጵያን የሚነካ አዋርዶም ለአዋራጅ አሳልፎ የሚሰጥ መጨረሻው የአጋንንት መኖሪያ ወደሆነው ሲዖል መውረድ ነው፤ በዚያም ሥፍራ እንደነመለስና ግብረ አበሮቹ በገሃነማዊ እሳት እየተለበለበ እስከዘላለሙ ይኖራል።”

## እንደመደምደሚያ፡-

- ከ31 ዓመታት በኋላ ሀገራችን ለቀጣዩ ዙር የአፍሪካ ዋንጫ በማለፏ እንኳን ደስ ያለን!
- ጥቅምት ወትሮም ንፋሳም ነው - የሰሞኑ ግን ለየት ይላልና ለበጎ ያድርግልን!
- ይህች የ2005ዓ.ም እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ እንድትሆን መልካም ፈቃዱ ይሁንልን!
- ይሔን ገና ከአሁኑ በጥቅምት አናት የሚበሳ የፀሐይ ሙቀት ጌታ ይገስጽልን!
- የሁለት ቀዳማዊት እመቤቶች ባለቤት ያደረገንን የእትዬ አዜብ ጎላን ማነው መስፍንን እልህ ያብርድልን! የተሠወረውን ልቧንም መልሶ ትምክህቷን ይውሰድላት!
- እያቃጠለ የፈጀንን የኑሮ ውድነት ፈጣሪ መላ ይበልልን!
- በሀገራችን እጅግ እየበዛ የመጣውን የዕብድ፣ የለማኝና የሰካራም ቁጥር አንድዬ ልጓም ያብጅልን!
- ጥራቱ ጠፍቶ ገደል የገባውን የትምህርት ሥርዓት እግዜሩ አንድ ይበልልን!
- በገንዘብ ፍቅር ያበደውን ነጋዴና የመንግሥት ባለሥልጣን አቅል ይስጥልን!
- በሀገራችን የሠፈነውን ሙስና ጠራርጎ ያጥፋልን!
- …